በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፩

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ታህሳስ ፱ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.**

# <u>መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፩</u>

- የሩትና የኑኃሚን ታሪክ የትውልድ ሁሉ ታሪክ ነው፡፡ ኑኃሚን የእግዚአብሔርን ሕግና የነቢያትንም ትንቢት ጠንቅቃ ስለምታውቅ እንደ አይሁዳዊነትዋ ብዙ በረከት ተትረፍርፎላታል፡፡
- ኑኃሚን ስለ ነገረ ድኅነትና እግዚአብሔርም ከአባቶችዋ ጋር ስለ ገባው ቃል ኪዳን ሰምታ ነበር፡፡
- በመከራም ጊዜ ከይሁዳ ሸሽታ ወደ ሞዓብ ሄደች፡፡ ይህም በመከራ ጊዜ እግዚአብሔርን ትታ ለሥጋዊ ምቾትዋ ወደ ዓለም የምትሸሽ ነፍስ ምሳሌ ነው፡፡
- በየዘመናቱ (ትውልዱ) ኑኃሚንም ሆኑ ሩት ይኖራሉ፡፡ ሩት ከአሕዛብ ወገን በሆነ በአባትዋ አገር በሞዓብ ያደገች ብትሆንም ስለ ሕያው እግዚአብሔር ነገር ትሰማ ነበር፡፡
- በእምነትም ሥጋ የለበሰውን የእግዚአብሔርን ቃል ለመገናኘትና እረፍትና እርካታን ለማግኘት ወደ ቤተልሔም ሄደች፡፡
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት፡፡›› <u>*ሉቃ 2፡34፡፡*</u> ይሆን ዘንድ መጣ፡፡
- ኑኃሚን የእግዚአብሔርን ጸጋ በመተውዋ ስትረሳ ሞዓባዊትዋ ሩት ግን በእግዚአብሔር ላይ በነበራት እምነትዋ የተነሳ ከፍታን አግኝታለች፡፡
- እንደ ታልሙድ የመጽሐፈ ሩት ጸሐፊ ነቢዩ ሳሙኤል ነው፡፡
- በመጽሐፈ ሩት ተጽፎ የምናገኘው ታሪክ የተፈጸመውም በዘመነ መሳፍንት ነው፤ የተጠቀሰውም ረሐብ በጌዴዎን ዘመን የነበረ ነው፡፡<u>*መሳ 6፡1፤11፡፡*</u>አንዳንዶች ሩት በካህኑ በዔሊ ዘመን የነበረች ሴት ናት ይላሉ፡፡
- ሌሎች ደግሞ ይህ ታሪክ የተጻፈው በንጉሥ ዳዊትና በሞዓቡ ንጉሥ መካከል የነበረውን ግኑኝነት ለማጠንከርና የዳዊት የሴት አያቱ ከሞዓባውያን ወገን እንደሆነች ለማመልከት ነበር ብለው ያምናሉ፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፩

- ይህ መጽሐፍ ሩት ከቃረመችው እርስዋና አማችዋ ይበሉ ዘንድ እንደሆነ ስለሚያስረዳን ከመከር በዓል (ጰንጠቆስጤ) የሚያያዝና በዚህም በዓል የሚነበብ ነበር፡፡
- ይህ መጽሐፍ የመከር መጽሐፍ የተባለው በሃይማኖት አሕዛብ የነበሩ አዲስ አዝመራ በሆነችው በሩት የተነሳ በእግዚአብሔር አምነው አሸተው አፍርተው ስለተገኙ ተቀባይነት እንዳገኙ ስለሚያስተምረን ነው፡፡
- ‹‹እውነተኛ የሕይወት መብል›› የተባለው ክርስቶስን በትውልድ ሐረግዋ በመያዝ አማችዋን ኑኃሚንን ደስ አሰኝታታለች፡፡
- በመጽሐፍ ቅዱሳችን በአሕዛብ ሴቶች ስም የተጠራ መጽሐፍ መጽሐፈ ሩት ነው፤ ሩት ከአሕዛብ ሴቶች ልቃ ተገኝታለችና፡፡
- ከአሕዛብ ወገን ብትሆንም የዓለም መድኃኒት በሆነው በጌታችንም የትውልድ ሐረግ (ከሰው የነሳው ሥጋና ደም የትውልድ ሐረግ ቁጥር) ተጠቅሳ እናገኛታለን፡፡ ‹‹ሰልሞንም ከራኬብ ቦኤዝን ወለደ፤ ቦኤዝም ከሩት ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፤እሴይም ንጉሥ ዳዊትን ወለደ። ንጉሥ ዳዊትም ከኦርዮ ሚስት ሰሎሞንን ወለደ›› ***ማቴ 1:5፡፡***
- መጽሐፉ ለሰው ነፍስ የሆነው ‹‹ፍጹም እርካታ›› ከእውነኛው ሙሽራ ከቦዔዝ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ጋር ከሆነ ውኅደት የተገኘ መሆኑን ያስረዳናል፡፡
- በመጽሐፈ ሩት ተደጋግመው የምናገኛቸው ዘመድ፣ አማች የሚሉ ቃላቶች በጌታችንና በሕዝብና በቤተ አሕዛብ መካከል እንደ ቤተሰብ የሆነ የቅርብ ግኑኝነትን የሚያመለክት ምሳሌ ነው፡፡
- በእምነትና በሥነ ምግባር መካከል ያለውን መቀራረብ ብሎም በኑኃሚንና በሩት፣ በቦዔዝና በሩት መካከል የነበረውን ንግግር በማንሳት በንግግር በአግባብ መግባባት ከሚያምኑት ወገን ምን ያህል የሚጠበቅ ምግባር እንደሆነ ያስተምረናል፡
- መጽሐፉ አንዳንድ የአይሁድ ባሕልና ትውፊትንም እያነሳ ሩትን በሕይወት የምትኖርና የምትመላለስ አድርጐ በምሳሌነት ያስነብበናል፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፩

***ዓለምና ባዶነትዋ***

- አቤሜሌክ ‹‹እግዚአብሔር ንጉሤ ነው›› ማለት ሲሆን ከሚስቱ ከኑኃሚን (በልብ የተባረከች)፣ ከመሐሎን (ድርቅ ወይም በሽታ) እና ከኬሌዎን (ውድመት ወይም ፍርስራሽ) ጋር በይሁዳ ከነበረው ረሐብ የተነሳ ሸሽተው ወደ ሞዓብ ምድር መጥተው በዚያው ተቀመጡ።
- ይህም አቤሜሌክ ቤተ ክርስቲያንን (ቤተ ልሔም) መከተል - ማጣት ናት፣ ክርስቶስንም መከተል ክስረት ነው ብሎ የሚያስብ ሰውን ይመስላል።
- እርሱም ከሚስቱ (አካሉ) እና ችሎታውንና እቅሙን ከሚወክሉ ከሁለቱ ልጆቹ ጋር ወደ ሞዓብ ሄደ፤ ዓለምም የሥጋ ፍላጎቱን የምታሟላለት፣ አቅሙንም እንዲያሳድግ የምትረዳው አድርጎ ቢያስብም ነገሩ ሁሉ ራሱን ሳይቀር ሁሉን በማጣት ተጠናቋል።
- አቤሜሌክ በእግዚአብሔር ጥላ ሥር ከማረፍ ይልቅ በሞዓብ ንጉሥ ጥበቃ ሥር ሊኖር ወደ ሞዓብ ወርዷልና ስሙ እንደ ግብሩ አልነበረም። ስሙን ሳይገባው ተጠርቶበታልና ድርቅ - መሐሎንና ኬሌዎንን - ፍርስራሽ ወለደ።
- አቤሜሌክና ቤተሰቦቹ ‹‹በዘመንህ ሁሉ ለዘላለም ሰላምና ልማት ለእነርሱ አትሻ።›› ***ዘዳግ 23፡6፡፡*** በማለት ከማያምኑ ጋር እንዳይተባበሩ፣ ከእውነትም ፈቀቅ ይሉ ዘንድ ከሚመሯቸው እንዲጠበቁ የነገራቸውን ረስተው የተስፋይቱን ምድር ትተው ወደ እንግድነት አገር ጥገኝነት ፈልገው ገቡ።
- በዚህም የተነሣ ኑኃሚን ባልዋ ሞተባት ልጆችዋም ሞዓባውያንን አገቡ፤ ከሕጉም ተጻራሪ በሆነ መንገድ በዚያው ኖሩ። ‹‹ከእነርሱም ጋር አትጋባ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጁ አትስጥ፥ ሴት ልጁንም ለወንድ ልጅህ አትውሰድ። እንዳይከተለኝ ሌሎችንም አማልክት እንዲያመልክ ልጅህን ያስታልና የእግዚአብሔርም ቍጣ ይነድድባችኋል፥ ፈጥኖም ያጠፋችኋል።›› ***ዘዳግ 7፡3-4***፣ ‹‹ በዚያች ምድር ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን እንዳታደርግ፥ እነርሱ አምላኮቻቸውን ተከትለው ባመነዘሩና በሠዉላቸው ጊዜ እንዳይጠሩህ፥ ከመሥዋዕታቸውም እንዳትበላ፥ ሴት ልጆቻቸውንም ከወንድ ልጆችህ ጋር እንዳታጋባ፥ ልጆቻቸውም አምላኮቻቸውን ተከትለው ሲያመነዝሩ ከአምላኮቻቸው በኋላ ሄደው አመንዝረውም ልጆችህን እንዳያስቱ ተጠንቀቅ።›› ***ዘጸ 34፡15-16፡፡***

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፩

***ዓለምና ባዶነትዋ***

- እጅግ የተመረረችው ኑኃሚን ወደ ይሁዳ ለመመለስ መፈለግዋ፤ ከእውነት ወጥተው ወደ እውነትና ቤተ ክርስቲያን መመለስ የሚፈልጉትን ሰዎች ይመስላል፡፡
- ኑኃሚን ምራቶችዋን (የልጆችዋን ባሎች) በየዋሕነትና በቅንነት የጠበቀቻቸው ስትሆን ይህንም ያደረገችው ለነርሱ ስለነበራት ፍቅር ነበር፡፡
- በዚህም የተነሣ ወደ እናቶቻችሁ ቤት ተመለሱ በእኔና በሞቱት እንዳደረጋችሁ እግዚአብሔር ቸርነትን ያድርግላችሁ አለቻቸው፡፡ ***ሩት 1፡11-13፡፡***
- ይህንኑ ጥያቄ ሦስት ጊዜ ከጠየቀቻቸው በኋላ ዖርፋ የፍቅር እንባ አፍስሳ አልቅሳ ወደ ዘመዶችዋ ቤት ተመለሰች፡፡ በዚህም ዖርፋ የሰውን የመታመን ደረጃ የምታስተምረን ስትሆን ሩት ደግሞ ከሰው መታመን በላይ ማለፍን ታስረዳናለች፡፡ ሩት ይህን ለማድረግ የበቃችው በእምነትና በእምነትዋ ጽናት ነበር፡፡
- ሩት የአማንያን መንፈሳዊ አባት ይሆን ዘንድ ከካራን ወጥቶ እግዚአብሔርን ለመከተል ከነዓን የገባውን የአብርሃምን እምነት ይዛ ተገኝታለች፡፡
- ሩት ከሞዓብ ሸሽታ በመውጣት እውነተኛውን እግዚአብሔርን ለማምለክ በመምረጥዋ ለአማንያን የንጉሡ ሐረግ ቁጥር ውስጥ ገብታ ተቆጥራለች፡፡ ከዘርዋም የነገሥታት ንጉሥ የሆነው በሥጋ ተወልዷል፡፡
- ኑኃሚን በተሰበረና በተመረረች ልብ በነፍስዋ ዝላ ወደ ይሁዳ ተመልሳለችና የኑኃሚንና የሩት ወደ ይሁዳ መመለስ በቤተልሔም ታላቅ መታወክ ሆነ፡፡ ኑኃሚንም ስለኃጢአትዋ የመለኮትን ምሕረት ፈለገች፡፡
- ኑኃሚን የገደለ ይገደል የምትለውን የቀደመውን ዘመን የምታስታውስ ምሳሌ ስትሆን ሩትና ቦዔዝን ማግባትዋም ደግሞ መበለትነትን ያስወገደ፣ የንጉሡን የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድና የተስፋችንንም መታደስ ያመለክታል፡፡

# <u>መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፩</u>

## ***<u>ክርስቶስና እርካታ - መጽሐፈ ሩት 2 - 4</u>***

- ሩት ኑኃሚንን ተከትላ ወደ ቤተልሔም በመምጣት ወደ ቦዔዝ እርሻ በመግባት እንድትቃርም (የወደቀውን እህል ለመሰብሰብ) መጠየቅዋ አሕዛብ አምነው ከቤተልሔም (ቤተ ክርስቲያን) ማኅበር መደመራቸውን ያመለክታል፡፡
- ኑኃሚን በሕግ መጽናትዋ ከመንፈሳዊነት አለመለየትዋንና መንፈሳዊነትን ችላ አለማለትዋን ያስተምረናል፡፡
- ሩት አስቀድመው አባቶችና ነቢያቱ የደከሙበትን ፍሬ ለመሰብሰብ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ (እውነተኛው ቦዔዝ) እርሻ ገባች፡፡
- ከእርሻውም ሙሉነትን የሚያድለውን ‹‹የሕይወት መብል›› የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ቃረመች፡፡
- ሩት ወደ ቤተልሔም ስትገባ የሚዛመዳትን ቦዔዝን ተገናኘችው፡፡ እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ በሥጋና በነፍስ ዘመድ የሚሆነንን ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንገናኘዋለን፡፡
- ቦዔዝ (ብርታት) ሲሆን እርሱም ከሲዖል ባርነት ነጻ ያወጣንን ኃይላችንና ብርታታችን የሆነውን ክርስቶስን ይመስላል፡፡ ኃያል ሰው የሚባለው ኦሪትና ነቢያትን ሳይሽር ሕግን የሚፈጽም ‹‹ለእኛም ሁልጊዜ ድል በመንግሥቱ የሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ የሚገልጥ አምላክ - ኢየሱስ ክርስቶስ›› እንጂ የጦርነት ሰው - ተዋጊ ብቻ አይደለም፡፡
- እንግዳይቱ ሩትም ከአማትዋ ከኑኃሚን ፈቃድ በመውሰድ እህል ለመቃረም ስትሔድ ያለእረፍት የምትሠራ እንደነበረች <u>*ሩት 2፡7*</u> የተጻፈልን ‹‹አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና። እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ።›› <u>*ዮሐ 4፡37-38፡፡*</u> የተባሉትን የምትወክል ስትሆን ኑኃሚን በቤት መቅረትዋ አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመቀበል የዘገዩ የሚያስተምረን ነው፡፡
- ቦዔዝም ‹‹ይህች ቆንጆ የማናት?›› ብሎ ጠየቀ፡፡ ምላሹም ከሞዓብ የመጣች ባል የሌላት ናት የሚል ነበር፡፡ ሕዝብና አሕዛብ መምጣቱን የሚጠባበቁትን ሙሽራውን ክርስቶስን ይጠብቁት እንደነበር ያስተምረናል፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፩

***ክርስቶስና እርካታ - መጽሐፈ ሩት 2 - 4***

- ሩት ወደ እርሻው ስትመጣ ቦዔዝ እንግዳይቱ ሩትን እግዚአብሔር በማደጎ የሚያሳድግሽ ልጄ ፣ ወደ ገረዶቹ፣ ወደርሱም (ክርስቶስ)፣ ወደ ጎበዛዝቱ (ቅዱሳኑ) እንድትጠጋ፣ ጎበዛዝቱ ከቀዱት ውኃ (በቤተ ክርስቲያን በኩል ከመንፈስ ቅዱስ ምንጭ) እንድትጠጣ (***ዮሐ 3:37::)*** አነጋገራት። ***ሩት 2:8-9::***
- ሩት ፍጹም የሆነው ፍቅር በልብዋ ሲፈስ ስጦታው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነጻ ስጦታ ምልክት መሆኑን ለማመልከት በምድር ላይ በግምባርዋ ተደፍታ ሰገደች። ***ሩት 2:10::***
- ሩት በትሕትና ሆና ቀርባለችና የምስጋናን ቃል ለመስማት ታደለች። ***ሩት 2:11::***
- ሩት በቅድሚያ ሰይጣንንና የበደልን ሕይወት ትታ አስቀድማ ወደ ማታውቃቸው ወገኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን ገስግሳለችና ሞገስን አገኘች።
- ቦዔዝም ቀርባ ከሚበላው እንድትካፈል - ከቅዱስ ሥጋውና ደሙ ማዕድ ከቅዱስ ቁርባን እንድትካፈል ***(2:14)*** እና በነዶው መካከል ማንም ሳያስጨንቃት እንድትቃርም ጋበዛት ፈቀደላትም። ***(2:15-16***)
- በአጠቃላይ ይህ ንግግር የክርስቶስን ፍቅርና ስጦታውን በትሕትና ለሚራመዱ ሩትን ለሚመስሉ እንደሚታደል የሚያስረዳን ነው።
- ሩትም ቃርሚያውን ከሰበሰበች በኋላ ወቅታ፣ ገብሱን ከገለባው ለይታ ለአማትዋና ለርስዋ ለአምስት ቀን የሚበቃቸውን ለኑኃሚን ሰጠቻት። ይህም ነፍስ በመንፈሳዊው ፍቅር ከቦዔዝ (ክርስቶስ) ጋር መገናኘትዋን በመውቂያው በመስቀሉ ተመትታ (ተማርካ) የሚያረካ የመንፈስን ፍሬ ማፍራትዋን ያመለክተናል።
- የኑኃሚንን ልብ የማረከው ግን ከቃርሚያ የተገኘው ገብስ ሳይሆን ቦዔዝ ነበርና ከገረዶቹ ጋር ከእርሱ እርሻ በቀር ከሌላ እንዳትቃርም አስጠነቀቀቻት፤ እነዚህም የቦዔዝ (ክርስቶስ) ገረዶች የተባሉት ቅዱሳን ሲሆኑ ከነርሱ ጋር መውጣትዋም ከቅዱሳኑ ጋር በሰማያዊ ደስታ ደስ እንዲላት (እንዲለን) የሆነውን ያስተምረናል። ***(2:20)***

ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org